# ብርሃኑ ፣ የብተና ካህኑ

ለማማ ኢትዮጵያ ፣ ውለታዋን ከፋይ
የናት አባቶቹን ፣ አደራ ተቀባይ
ምነው ፣ ባገሩ ላይ ፣ ወንድ ፣ በቅሎ እማናይ
አልገዛም የሚል ፣ ጀግና ፣ እንደ በላይ
መከነች ወይ ፣ አገር ፣ ወይስ ነው ፣ ሾተላይ?
እንዲህ ለዘመናት ፣ አልወጣ አለች ፣ ፀሃይ ።

ተማርኩኝ የሚለው ፣ ሆኖ የታመመ
አጎብዳጁ በዝቶ ፣ ስልጣን ለተሾመ
ይነጋል ስንለው ፣ ቀኑ እየጨለመ
በነ ፣ ሆድ አምላኩ ፣ ትግሉ ተራዘመ ።

የበላንን ትተን ፣ ያልበላንን አከን
አገር ወዳድ ፣ ንቀን ፣ ምሁሩን አምልከን
ሺዎች ፣ ደም ገብረው ፣ ትግል ዳግም ፣ ሲመከን
ምነው የማንቆጭ ፣ የማንብከነከን ?

ትግሉን ሲያደርጉት ፣ እንደ ፣ ቬጋስ ቁማር
ካሳለፍነው ዘመን ፣ ዘወትር አንማር
እሬት እያላሱን ፣ ማጣጣም እንደ ማር
ሁሌም ፣ አድሮ ቃሪያ ፣ ተመልሰን ቅርቃር
ድግሱን እያየን ፣ ላገራችን ተዝካር
ዛሬም አሜሩሪ ፣ የአጥፊዎች አጋር ።

ከልጅነት እድሜ ፣ እስከ ሽምግልና
ውሸት አያልቅበት ፣ የለው ስብዕና
ዘወትር ቅዠቱ ፣ ስልጣንና ዝና
ክህደት የተጣባው ፣ ወላዋይ ቁመና
አልፋታህ ብሎት ፣ የስልጣን ምርቃና
ዛሬም ይፏልላል ፣ ባገር ሰው ጠፋና ።

ዳፍንት ለተያዘ ፣ ለታወረ ዐይኑ
ተነግሮ እማይሰማ ፣ ለጆሮ ድፍኑ
በዳበሳ ተጓዥ ፣ ለየዋህ ምስኪኑ
ሲፈራርስ ሳይሆን ፣ ዛሬ ነው ፣ ማዘኑ
አድርባይ ባይጠፋም ፣ እንደየ ዘመኑ
ያጅሬው ይከፋል ፣ ከሁሉም ሚዛኑ
ብርሃኑ የነካው ፣ የብተና ካህኑ
እስኪ አንድ ፣ ይጠራ ፣ ያልተበታተኑ
ሲነጋም አልታየ ፣ ሲመሽ እንጂ ፣ ቀኑ ።

ታዛቢው

June 13, 2019